# የድጓ ማስመስከር ትምህርት ሥነ ትምህርታዊ ፋይዳ በቅድስት ቤተ ልሔም፤ ገላጭ ጥናት

**አባ ጴጥሮስ ጥበቡ**[1] **እና ማረው ዓለሙ**[2]

## አሕጽሮተ ጥናት

በደቡብ ጎንደር ከደብረታቦር አቅጣጫ ወደጋይንት ነፋስ መውጫ ከተማ ለመድረስ ፳ ኪ.ሜ. ሲቀር ወደቀኝ ታጥፎ ባለው የጠጠር መንገድ በ፳፫ ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ጥንታዊቷ ቅድስት ቤተ ልሔም ትገኛለች። መንገዱ በበጋም ኾነ በክረምት ጊዜ ከትንሽ እስከ ትልቅ መኪና ያለችግር ለማሽከርከር ያስችላል። ቅድስት ቤተ ልሔም[3] ከታነጸች ረዥም ዕድሜ እንዳስቆጠረች የሚገልጹ የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ቅርሳዊ አስረጂዎችን በቦታው ማስተዋል ይቻላል። ቅርሶቹን በትክክል ለመረዳት ብሎም ከእነሱ ተጠቃሚ ለመሆን ግን የተለያዩ ባለሙያዎችና ተመራማሪዎች የጋራ ጥረት ይጠይቃልና በዚህ ረገድ መትጋት ያስፈልጋል። ቅድስት ቤተ ልሔም ዘመን ተሻጋሪ የሆኑ የጥበባት ውጤቶች ባለቤት ብቻ ሳትሆን ከረጅም ጊዜ ጀምሮ የድጓ ማስመስከሪያ ትምህርት ቤትም ናት፤ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ሥርዐት ለመሪጌትነት ከሚያበቁት የትምህርት ዘርፎች መካከል አንደኛው ድጓ ሲሆን፣ ቅድስት ቤተ ልሔም የድጓ ምስክር ትምህርት ቤት ናት[4]። የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት ሥነ ትምህርቱን የሚመለከት ነው። ስልቱ ገላጭ ሲሆን፣ የተኖረ ልምድ/ተመክሮ[5] (lived experience)፣ ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅና ተዛማጅ ድርሳናት የጥናቱ ዋና የመረጃ ምንጮች ናቸው። ቅበላ፣ መማር-ማስተማር፣ አስተዳደርና ምረቃ የጥናቱ ትኩረቶች ናቸው። የተማሪው ቅበላ የመግቢያውን ፈተና ማለፍ የግድ የሚያደርግ ሲሆን፣ የፈተናው ዓይነትም መስፈርት-ተኮር ነው። በመግቢያው ፈተና የሚለካው የግለሰብ ብቃት እንጂ የቡድን ብቃት ወይም ችሎታ አይደለም። መማር-ማስተማሩ የአድራሽ ተማሪን፣ የድጓ መምህሩንና የመላውን ተማሪዎች ሦስት ጎንዮሽ መስተጋብር በግልጽ አሳዩ፣ እጅግ ሲበዛ አሳታፊና ተግባር-ተኮር ነው። በሌላ አገላለጽ አንድ ለአንድና አንድ ለብዙ ዓይነት መስተጋብር አለው፤ ትምህርቱ የሚጀመረው በመምህሩ ሳይሆን በአድራሽ

---

1 ዶ/ር፣ በኢ.ኦ.ተ.ቤ. ሰሜን አሜሪካ የኒውዮርክና አካባቢው ሀገረ ስበክት ሊቀ ጳጳስና የሲኖዶሱ ዋና ጸሓፊ፣ abagtibebu@gmail.com

2 ዶ/ር፣ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል ተባባሪ ፕሮፌሰር፣ marewalemu@gmail.com

3 "የቅድስት ቤተ ልሔም ቤተ ክርስቲያን ሕንጻ በልዩ ልዩ የሐረግ ቅርጽ ያጌጠች፣ እጅግ በሚያስደንቁ ጥርብ ድንጋዮች የተገነባች፣ ባለ፲፪ ቤተ መቅደስ፣ በኢትዮጵያ በአሁኑ ሠዐት አምሳያ የሌላት፣ ቅርፀ ሞላላ፣ ወይም የአራት መዓዘን ሰቀላ ቅርጽ ያላት ስትሆን፣ ግንብዋም ሆነ ጣራዋ በጥርብ ድንጋዮች ተዋቅሮ የተሠራ ነው።" (ገሪማና ሌሎች 2009 ዓ.ም. ገጽ 118)።

4 "በግራኝ መሐመድ ጦርነት ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ብዙ መጻሕፍት ስለተቃጠሉባትና ድጓም በደረሰው ቃጠሎ ስለወደመ በቀላሉ ሊገኝ አልቻለም፤ በኋላ ግን አጼ ሠርፀ ድንግል ድጓ የሚገኝበትን ደብር ሲያፈላልጉ በበጌምድር ውስጥ ጉና ተራራ አጠገብ በምትገኘው በቅድስት ቤተ ልሔም ደብር የሊቁ ልሳነ ዕፍረት ድጓ ተገኘ። ከዚህም የተነሳ ንጉሡ ቤተ ልሔም የድጓ ማስመስከሪያ እንድትሆን በመፍቀዳቸው እስከአሁን በዚሁ ትታወቃለች።" (ገሪማና ሌሎች፣ 2009 ዓ.ም.፣ ገጽ 118)።

5 ከዚህ ጥናት አቅራቢዎች አንደኛው በአብነት ትምህርት ቤት ሰፊ ተመክሮ አላቸው።

ተማሪ ነው፤ አድራሹ ተማሪ ለመማር ዋናውን ድጓ ያዜማል፡፡ መምህሩ በጽሞና እየተከታተሉ ያርማሉ፡፡ ሌሎች ተማሪዎች አድራሹን ተማሪና መምህሩን እየተከታተሉ የየግል ድጓቸውን ያመለክታሉ፤ ያርማሉ፤ ያልገባቸውን ይጠይቃሉ፤ ብሎም ይማራሉ፡፡ በዚህም አድራሹ ተማሪ በአንድ ጊዜ የመማርና የማስተማር ጥንድ ሥራዎች እንደሚሠራ ልብ ይሏል፤ እሱ ከመምህሩ ይማራል፤ ሌሎች ተማሪዎች ደግሞ ከአድራሹ ተማሪና ከመምህሩ ይማራሉ ማለት ነው፡፡ የትምህርት ቤቱ አስተዳደራዊ መዋቅር ደግሞ በኹለት የተከፈለ ነው፤ የአስተዳደር ክፍሉ በመላው ተማሪዎች በተመረጠ ተማሪ ሲመራ፣ አካዳሚክ ክፍሉ በድጓው መምህር ይመራል፡፡ ድጓ ለማስመስከር የመግቢያ ፈተና እንዳለ ኹሉ፣ ለመመረቅም የመውጫ ወይም የማጠናቀቂያ ፈተና አለ፡፡ ፈተናው የሚካሄደው በተራ ወንበር በግል በሊቃውንቱ መካከል ነው፤ በተራ ወንበር መድረክ አግኝቶ ለመፈተን ከተማሪዎች ቍጥር ብዛት የተነሣ ከሦስት እስከ አራት ወራት ተራ ሊያስጠብቅ ይችላል፡፡ ፈተናውን ተፈትኖ ላለፈ ተማሪ፤ (፩) ጠንቅቆ አመልክቶና አርሞ በሚያቀርበው በማተሚያ ቤት በታተመ የድጓ መጽሐፍ[6] የመጀመሪያና የመጨረሻ ገጾች ጎዳግ ላይ ስለትክክለኛነቱ የምስክሩ መምህር ማኅተም ይደረግለታል፤ (፪) የድጓ ትምህርቱን በቅድስት ቤተ ልሔም አጠናቆና ፈተናውን አልፎ መመረቁንና ጉባኤ ዘርግቶ ድጓ ማስተማር የሚችል መሆኑን የሚገልጽ "ቃለ በረከት" የሚባል ድብዳቤ ለመጣበት ደብር ይጻፍለታል፤ (፫) በማተሚያ ቤት የታተመ የምስክር ወረቀት (ዋናው ዲግሪ ለማለት ይቻላል፡፡) የተማሪው ፎቶ ተደርጎበት በማኅተም ተረጋግጦ ይሰጠዋል፡፡ በዚህ ጥናት የተማሪን ቅበላ፣ አስተዳደር፣ መማር-ማስተማርና ምረቃ እውነተኛ መልክና ቅርጽ ይዛ ለዘመናት አጽንታ ከዘለቀችው ከቅድስት ቤተ ልሔም የድጓ ማስመስከሪያ ትምህርት ቤት ዘመናዊዉ ትምህርት የሚማራቸው ብርቱ ቁምነገሮች ተለይተው ተጠቁመዋል፡፡

**ቁልፍ *ቃላት*፡-** አድራሽ፣ ድጓ፣ ድጓ ማስመስከር፣ ሥነ ትምህርታዊ ፋይዳ፣ ሦስት ጎንዮሽ መስተጋብር፡፡

## *መግቢያ*

ኢትዮጵያ የረዥም ጊዜ[7] ባለታሪክ ሀገር ናት [በሞላና ሌሎች (2022) የተጠቀሱት ፓንክረስት፣ 1972፤ ተሾመ፣ 1979]፡፡ ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ፪ኛው ክፍለ-ዘመን መጽሐፍ ቅዱስ ከተተረጎመባቸው ጥቂት ቋንቋዎች መካከል ኹለቱ የአፍሪቃ ቋንቋዎች የኢትዮጵያው ግእዝና አሮጌው ቅብጥ (ኮፕቲክ) የግብፅ ቋንቋ ናቸው፡፡ ከዚህም ሌላ ኢትዮጵያ የራሷ ፊደልና የዘመን አቈጣጠር ያላት በማንም ሀገር ቅኝ ያልተገዛች ነጻ ሀገር ናት (ያሬድና ሌሎች፣ 2020)፤ ፍርድይወቅና እርጥባን (2018) እንደሚገልጹት ከሳሀራ በታች ከሚገኙት ሀገሮች ብቸኛዋ ጥንታዊ የጽሑፍ ባህል

6 እስከ ንጉሡ ዘመን ድጓ ለማስመስከር ድጓውን በብራና ላይ በእጅ መጻፍና ጠንቅቆ ማመልከት የግድ ነበር (ሀብተ ማርያም፣ 1963 ዓ.ም.)፡፡

7 “እውነተኛው የኢትዮጵያ ታሪክ በስፋት ሲታይ እስከ ስድስት ሺ ዓመት የሚደርስ፣ በጠባቡ (ከመንግሥት ምሥረታ አንጻር) ሲታይ ደግሞ እስከ ኹለት ሺ ኹለት ዓመት ተኩል የሚሆን ነው፡፡” (ባሕሩ፣ 1984 ዓ.ም./1992፤ገጽ 10)፡፡

ያላት ሀገር ኢትዮጵያ ናት፤ ኢትዮጵያ የዕውቀትና የጥበብ መሠረት በኾነችው በኢ.ኦ.ተ.ቤ. አማካይነት ከ፲፯፻ ዓመት የሚልቅ ጥንታዊ የትምህርት ሥርዐት ያላት ሀገርም ናት፡፡ በኢትዮጵያ እ.አ.አ. በ፲፱፻፰ የዘመናዊ ትምህርት እስኪተዋወቅ ድረስ፣ ከ፳ኛው ክፍለ-ዘመን ጀምሮ የቤተ ክርስቲያን (የአብነት ትምህርት ቤት) ትምህርት ብቸኛው የትምህርት ተቋም ነበር፡፡ በዚህም የኢት.ኦ.ተ.ቤ. የሀገሪቱ የትምህርት ሚኒስቴር ኾና ማይምነት ሥር እንዳይሰድ ስትሠራ ኖራለች (መርሻ፣ 2011 ዓ.ም.)፡፡ በዚህም የማንበብ፣ የመጻፍ፣ የሒሳብ፣ የሥነ ጥበብ፣ የሥነ ሕንጻ፣ የሕግና አስተዳደር ወዘተ. ትምህርቶች ሲሰጡ ዘመናትን አልፈዋል፡፡ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ጥንታዊዉን ጥበባዊ ዕሴት በማቆየትና ከትውልድ ወደ ትውልድ የማስተላለፊያ መሣሪያ በመሆንም አገልግሏል፡፡

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረትም ከአብነት ትምህርቶች አንዱ የኾነውን የድጓ ማስመስከር ትምህርት መመርመር ነው፡፡ ጥናቱ የተካሄደው በደቡብ ጎንደር ታች ጋይንት በምትገኘው በቅድስት ቤተ ልሔም ቤተ ክርስቲያን ሲሆን፣ ዋና ዓላማውም ድጓ የማስመስከርን ትምህርት በመመርመር ሥነ ትምህርታዊ ፋይዳውን ማሳየት ነው፡፡ በጥቅሉ ከኢ.ኦ.ተ.ቤ. ጥንታዊ ትምህርትና በተለይ ደግሞ ከድጓ ጋራ በተያያዘ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ እስካሁን የተሠሩ ምርምሮች (ለምሳሌ፣ አታላይና ሰሎሞን፣ 2022፤ ቢንስ፣ 2005/2013፤ ቼሎት፣ 2009 [በቼሎት የተጠቀሱት፣ ኤፍሬም፣ 1971፤ ሃየርና ፍሪድሪክ፣ 1976፤ መንግሥቱ፣ 1970፤ ፓንክረስት፣ 1955]፤ ፍርድይወቅና እርጥባን፣ 2018፤ ግርማ፣ 1967፤ ኃይሉ፣ 1974፤ መንገሻ፣ 2021፤ መዝሙር፣ 2011፤ ጳውሎስ፣ 1976፤ ሰላምሰው፣ 2017፤ ሰጣርገው፣ 2004፤ [በሰጣርገው የተጠቀሰው፣ ታደሰ፣ 1970]፣ ሽሊሜ፣ 1992፤ ታደሰ፣ 1985፤ ተበጀ፣ 2018) ቢኖሩም አንዳቸውም ግን የድጓ ማስመስከር ትምህርትን ሥነ ትምህርታዊ ፋይዳ በትክክልና በግልጽ የመረመሩ ኾነው አልተገኙም፡፡ ብዙዎቹ ተመራማሪዎች (ለምሳሌ፣ ግርማ፣ 1967፤ ኃይሉ፣ 1974፤ ውቤ፣ 2018፤ [ሰጣርገው (2004) ያጣቀሳቸው፣ ታደሰ፣ 1970፤ ተሾመ፣ 1979]) የአብነት ሥርዐተ ትምህርቱን በጥቅሉ 'ዶግማና ቀኖና' ለውጥንና ፈጠራን የማያበረታታ፣ በደካማ የማስተማሪያ ዘዴ የሚካሄድ፤ በሚል ከመተቸት ባለፈ አዎንታዊ ፋይዳውን ለማሳየት ድፍረት ያገኙ አይመስሉም፡፡ በተለይም ድጓን ጨምሮ በውስጡ አራት ትልልቅ ዘርፎች ያሉት ዜማ ቤት ብዙም ትኩረት የተሰጠው አይደለም (ውቤ፣ 2018)፡፡ ይህም ለዚህ ጥናት ዋና መነሻ ምክንያት ኾኗል፡፡ ቅበላና አስተዳደር፣ መማር-ማስተማርና ምረቃ የጥናቱ ዋና ዋና ትኩረቶች ናቸው፡፡ የጥናቱ ስልት ገላጭ ሲሆን፣ ምልከታና ቃለ መጠይቅ (ከግንቦት ፳-፳፩፣ ፳፻፲፬ ዓ.ም በቦታው በአካል በመገኘት የመማር-ማስተማር ሂደቱን በማስተዋልና ተማሪዎችንና የድጓውን መምህር በተናጠል በመጠየቅ የተካሄደ ነው፡፡)፣ የተኖረ ተመክሮ፣ ተዛማጅ ድርሳናት ዋና ዋና የመረጃ ምንጮች ናቸው፡፡

**መጽሐፈ ድጓ**

መጽሐፈ ድጓ ታላቁ ኢትዮጵያዊ የዜማ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ፮ኛ ክፍለ-ዘመን በሦስት የዜማ ስልቶች፣ በሦስት ክፍልና በ፳፪ አርዕስት የደረሰው ከፍተኛ ድርሰት ሲሆን (ጳውሎስ፣ 1976፤ ታደሰ፣ 1985፤ ዘርዐ ዳዊት፣ 2011 ዓ.ም.)፣ ቅዱስ ያሬድ ከደረሳቸው ጸዋትወ ዜማዎች (ድጓ፣ ምዕራፍ፣ ዝማሬና መዋሥእት፣ ዐሥራ ዐራቱ ቅዳሴ) የመጀመሪያው ነው፤ ሲተረጎምም "ድጓ ለቤተ ክርስቲያን፣ የቤተ ክርስቲያን ትጥቋ፣ መቀነቷ" እንደማለት ነው። በዐማርኛ ቋንቋ ድእግግ፤ ማለት ትጥቅ ሲሆን፣ ድጓ፤ ማለት ደግሞ ትጥቋ ይሆናል (ገሪማና ሌሎች፣ 2009 ዓ.ም፤ ኅሐ ጽባሕ፣ 1988 ዓ.ም.፤ ዘርዐ ዳዊት፣ 2011 ዓ.ም.)። በኢ.ኦ.ተ.ቤ. የዓመቱን መዝሙር አጠቃሎ የያዘ ነው። በውስጡ የዓመቱን በዓላትና የሳምንታት መዝሙራት የያዘ መድበል ነው፤ በታላላቅ በዓላትና እሑድ፣ እሑድ፣ የሚደረስ የዜማ መጽሐፍ ነው፤ የግጥም መልክ ያለው የተመጠነና የተለካ አሰካክም ስላለው ድጓ እውነተኛ መዝሙር ነው፤ ጎደሎ የሌለው ፍጹም ድርሰት ነው፤ ይባላል (ሀብተ ማርያም፣ 1963 ዓ.ም.)። አየለ (2007) እንደሚገልጸው፣ ድጓ በግጥም መልክ የቀረበ ቢሆንም፣ የሥነ መለኮት፣ የፍልስፍና፣ የታሪክና የሥነ ምግባር ሐተታዎችም (passages) አሉት። በጽሕፈቱ ረቂቅነት፣ በምልክቶቹ ብዛት የተነሣም ድጓ ማለት ረቂቅ ማለት ነው፤ በሚልም ይገለጻል፤ ጽሕፈቱ የረቀቀ፣ የደቀቀ ማለትም ነው።

በመጽሐፈ ድጓ ውስጥ የታወቁት ቅዱስ ያሬድ የፈጠራቸው ሦስቱ መሠረታዊ ዜማዎች[8] ግእዝ፣ ዕዝልና ዓራራይ ብቻ ናቸው[9] (ገሪማና ሌሎች 2009 ዓ.ም፤ ሀብተ ማርያም፣ 1963 ዓ.ም.፤ ዘርዐ ዳዊት፣ 2011 ዓ.ም.፤ መርሻ፣ 2011 ዓ.ም.፤ ታደሰ፣ 1985፤)። የፊደል ቅርጽ የሌላቸው ዋና ዋና የዜማ ምልክቶቹ[10] (ኖታዎች) ደግሞ ስምንት ሲሆኑ፣ እነሱም (፩) ይዘት፣ (፪) ደረት፣ (፫) ድፋት፣ (፬) ሂድ፣ (፭) ቍርጥ፣ (፮) ርክርክ፣ (፯) ቅናት፣ (፰) ጭረት ናቸው (ገሪማና ሌሎች፣ 2009 ዓ.ም፤ ሀብተ ማርያም፣ 1963 ዓ.ም.፤ መርሻ 2011 ዓ.ም.)። እነዚህ ስምንቱ የዜማ ምልክቶች የራሱ የቅዱስ ያሬድ ሲሆኑ፣ ከእሱ በኋላ በመጡት ሊቃውንት የተጨመሩ (፱) ድርስና (፲) አንብር፤ የሚባሉ ኹለት የዜማ ምልክቶች አሉ። በዚህም መሠረት የድጓው የዜማ ምልክቶች በአጠቃላይ ፲ ናቸው፤ የዐሥሩ አውታረ በገና ምሳሌዎች ናቸው። መጽሐፈ ድጓ በጥራዙ ብቻ ሳይሆን በኃይለ ቃሉም ታላቅ ስለኾነ፣ ለዝማሬ እንዲመች በአራት ታላላቅ ክፍሎች ይከፈላል። እነሱም (፩) ዮሐንስ (በዜማው ከባድነትና በቍጥሩ ብዛት ከኹሉም ይበልጣል፤ ከመስከረም ፩ እስከ ኅዳር ፴ ባለው ጊዜ ውስጥ ይዘመራል።)፤ (፪) አስተምሕሮ (ከታኅሣሥ ፩

8 የኹሉም ሙዚቃዊ ኖታዎች፣ የእንሳስት ድምፆችና የዎፎች ዝማሬ ሳይቀር ከሦስቱ በአንደኛው ሊመደቡ እንደሚችሉ ይታመናል (ታደሰ፣ 1985)።

9 ግእዝ በአብ፣ ዕዝል (በግእዝ ሕዙል) በወልድ፣ ዓራራይ (በግእዝ አራኅራኂ) በመንፈስ ቅዱስ ይመሰላል (ሀብተ ማርያም፣ 1963 ዓ.ም.)።

10 "ምልክት ለዜማ አገልግሎት ሲውል ዜማውን እንዴት ማዜም እንዳለብን ሊመራን፣ሊያስረዳን፣ ሊየሳውቅንና ሊያረጋግጥልን የሚችል ጠቃሚ ነገር ነው።" (ገሪማና ሌሎች፣ 2009 ዓ.ም፣ ገጽ 112)።

ጀምሮ አስከ ፋሲካ ባለው ጊዜ የሚዘመር ነው፡፡)፤ (፫) ጾመ ድጓ (በጾመ አርብዓ ወቅት በነግህ፣ በሠለስት፣ በቀትርና በሠርክ እንዲሁም እሑድና ቅዳሜ በሌሊት የሚዘመር ነው)፤ (፬) ፋሲካ (ከፋሲካ ጀምሮ እስከ ጳጉሜን መጨረሻ ባለው ጊዜ ውስጥ የሚዘመር ሲሆን፣ በውስጡ ልዩ ልዩ የበዓላትና የዘመናት ንዑሳን ክፍሎች አሉበት፡፡) ናቸው (*ገሪማና ሌሎች*፣ 2009 *ዓ.ም*፤ *ሀብተ ማርያም*፣ 1963 *ዓ.ም.*፤ *ዘርዐ ዳዊት*፣ 2011 *ዓ.ም.*)፡፡

በየትኛውም የዓለም ክፍል የማይገኝ በቅዱስ ያሬድ የተደረሰው መጽሐፈ ድጓ ከላይ እንደተገለጸው በተለያዩ ዓይነቶች የተከፋፈሉ መዝሙሮች አሉት፤ ዓይነቶቹም እንደየይዘታቸው ለተለያዩ ወቅቶች የተከፋፈሉ ናቸው፡፡ የመዝሙሮቹ ቍጥርም የአንደኛው ወቅት ከሌላኛው ወቅት ከሞላ ጎደል ተቀራራቢ ነው፡፡ በየቀኑ ከስምንት ሰዐት በላይ የሚወስዱ በመሣሪያ[11] እና ያለመሣሪያ የሚዘመሩ በአማካይ ፴[12] መዝሙሮች አሉ፡፡ እነዚህን መዝሙሮች በትክክል ሳያውቁ የተሟላ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መስጠት አይቻልም፡፡ ቢያንስ በትንሹ ከቅዱስ ያሬድ ዜማዎች አንዱን የሕዝባዊ አገልግሎት መስጫ ቅዳሴን[13] መማርና ማወቅ ያስፈልጋል (*መዝሙር*፣ 2011)፡፡ ስለኾነም የድጓ ማስመስከር ትምህርት በጥልቀት ከተመረመረ፣ በአግባቡ ከተመራና ከተያዘ ሥነ ትምህርታዊ፣ ፍልስፍናዊ፣ ጥበባዊ፣ ታሪካዊና ባህላዊ ፋይዳዎች ይኖሩታል፡፡ በተጨማሪም ከየትኛውም የዓለም ሀገራት ቱሪስቶችን የመሳብ ጠንካራ ኃይል እንደሚኖረው መገመት አያስቸግርም (ውቤ፣ 2018)፡፡

**የድጓ ማስመስከር ትምህርት የተማሪ ቅበላና አስተዳደር**

በኢ.ኦ.ተ. ቤ. የቤተ ክርስቲያን ሥርዐተ ትምህርት ንባብ ቤት፣ ዜማ ቤት፣ ቅኔ ቤትና መጽሐፍ ቤት፤ የሚባሉ የትምህርት ደረጃዎች አሉ (ሞላና ሌሎች፣ 2022)፡፡ የድጓ ትምህርት ዜማ ቤት፤ ከሚባለው ከኹለተኛ ደረጃ የትምህርት ሥርዐት ውስጥ ይገኛል፡፡ በኢ.ኦ.ተ.ቤ. ሥርዐተ ትምህርት መዝሙር በሰፊው የሚሰጥበት ትምህርት ቤት ዜማ ቤት፤ ይባላል፡፡ ዜማ ቤት አራት ዘርፎች ያሉት ሲሆን፣ እነሱም የድጓ ትምህርት፣ ዝማሬና መዋሥእት፣ አቋቋምና ቅዳሴ ናቸው፤ በወል ስማቸው ጸዋትወ ዜማ፤ ይባላሉ፡፡ በወል ስም ተጠቃለው ቢጠሩም ኹሉም በውስጣቸው በርካታ ንዑሳን ክፍሎችና አርዕስት አሏቸው (ቢኒስ 2013፣ *ሀብተ ማርያም*፣ 1963 *ዓ.ም.*፤ ተበጀ፣ 2018)፡፡

ከላይ እንደተገለጸው የድጓ ትምህርት በጥንታዊ የኢ.ኦ.ተ.ቤ. ሥርዐተ ትምህርት መሠረት ከፊደል እስከ ዳዊት መድገም ድረስ ያለው የአንደኛ ደረጃ (ንባብ ቤት)

---

11 "የማኅሌት *መሣሪያዎች* የሚባሉት ከበሮ፣ ጸናጽልና *መቋሚያ* ናቸው፡፡" (*ገሪማና ሌሎች*፣ 2009 *ዓ.ም. ገጽ* 124)፡፡

12 የዮሐንስ ፴፫፻፸፯፣ አስተምሕሮ ፴፬፻፹፬፣ ፋሲካ ፴፬፻፳፱ መዝሙሮች አሏቸው (*ሀብተ ማርያም*፣ 1963 *ዓ.ም.*)፡፡

13 "ድርሰቱ የሌሎች ሊቃውንት ኾኖ ዜማው ግን ሙሉ በሙሉ የቅድስ ያሬድ ነው፡፡" *ገሪማና* ሌሎች፣ 2009 *ዓ.ም.*፣ *ገጽ* 111)፡፡

ከተጠናቀቀ በኋላ ከሚመጡት የኹለተኛ ደረጃ ትምህርቶች አንዱ ቢሆንም የድጓ ማስመስከር ትምህርት ግን ከከፍተኛው ደረጃ ውስጥ የሚካተት ነው (አታሌና ሰሎሞን፣ 2022፤ ቼሎት፣ 2009)፤ [በቼሎት (2009) እና በጳውሎስ (1976) የተጠቀሱት ፓንክረስት (1962b]) እንደሚያስረዱት የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ዘርፎች የሚባሉት ዜማ ቤት፣ ቅኔ ቤትና መጽሐፍ ቤት ናቸው። ኹሉም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ዘርፎች የየራሳቸው ማስመስከሪያ ከፍተኛ ትምህርት ቤቶች አሏቸው፤ በዚህም መሠረት ቅድስት ቤተ ልሔም የድጓ፤ ዙር አምባ የዝማሬና መዋሥእት፤ ጎንደር ባታ የአቋቋም ማስመስከሪያ ከፍተኛ ትምህርት ቤቶች ናቸው (ገሪማና ሌሎች 2009 ዓ.ም.፤ ቼሎት፣ 2009፤ ተበጀ፣ 2018)።

በዚህ ጥናት በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ፣ በተዛማጅ ድርሳናትና በተኖረ ተመክሮ እንደተረጋገጠው የድጓ ማስመስከር ትምህርት በዘመናዊዉ ትምህርት በዩኒቨርሲቲዎች የሚታወቀውን የድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት እውነተኛ መልክ የያዘ ኾኖ ነው የተገኘው። ለዚህ በቂ አስረጂዎች አሉ፤ በመጀመሪያ የድጓ ማስመስከር ትምህርት የመጀመሪያም፣ የመጨረሻም የትምህርት ዕርከን አይደለም። በዘመናዊዉ የዩኒቨርሲቲ ትምህርት በቀጥታ ወደ ኹለተኛ ወይም ወደ ሦስተኛ ዲግሪ መርሐ ግብር መግባት እንደማይቻለው ኹሉ፣ ድጓ ለማስመስከር ወደ ቅድስት ቤተ ልሔም የድጓ ምስክር ትምህርት ቤት ለመግባት አስቀድሞ ቅኔ፣ ዜማ፣ ድጓ ወዘተ. መማርና ጠንቅቆ ማወቅ ግድ ይላል። በተለይም ድጓውን በሌሎች የድጓ ጉባኤ ቤቶች ለአራት ጊዜ ያህል መዝለቅ ግድ ይላል። ከዚህ በኋላ ወደ ቅድስት ቤተ ልሔም የድጓ ምስክር ትምህርት ቤት ለመግባት ፍላጎት ሲኖር፣ የድጓ ትምህርት ማጠናቀቅንና በዚህም ረገድ የግል ብቃትን የሚገልጽ ከድጓው መምህር የተጻፈ መሸኛ ደብዳቤ ይዞ መምጣት ያስፈልጋል። እንዲህም ኾኖ በቀጥታ መግባት አይቻልም፤ የመግቢያውን ፈተና ያለችግር ማለፍ ግድ ይላል። ለዚህም አስቀድሞ በሚወሰነው ቀን መሠረት የመግቢያ ፈተና ጥሪ ማስታወቂያ ይለጠፋል። ይህንንም ቀደም ሲል የቀደመውን የመግቢያ ፈተና አልፈው የድጓ ማስመስከር ትምህርት እየቀጠሉ ያሉት በቅድስት ቤተ ልሔም የሚገኙት ነባር ተማሪዎች በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ለሚገኙ ጓደኞቻቸው በስልክና በሚቻለው የመግባቢያ መንገድ ኹሉ ያሠራጩታል፤ ያዳርሱታል። ተማሪዎች ወደ ቅድስት ቤተ ልሔም የድጓ ማስመስከሪያ ትምህርት ቤት የመግባት ፍላጎት ሲኖራቸው በዓመት ውስጥ ሦስት ጊዜ (ከነሐሴ ፲፮-፴ ወይም ከግንቦት ፩-፲፫ ወይም ከታኅሣሥ ፳-፴) ማመልከት ይችላሉ (ሰላምሰው፣ 2017)።

የድጓ ማስመስከሪያ ትምህርት ለመከታተል የሚያስችለው ወይም የማያስችለው የመግቢያ ፈተና የሚዘጋጀው በኮሚቴ ነው። በቅድስት ቤተ ልሔም ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትና ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ካሉት ከተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ከመጡት መካከል በድጓው መምህር የሚመረጡት ዐምስት ነባር ተማሪዎች የፈተና አዘጋጅ ኮሚቴው አባል ይሆናሉ (ሰላምሰው፣ 2017፤ የቃለ መጠይቅ መረጃ)። በዚህም መሠረት የኮሚቴው አባላት ፈተና እንዲያዘጋጁ የሚነገራቸው በዋዜማው ሌሊት ከእንቅልፋቸው ተቀስቅሰው ነው። የዚህም ዋናው ምክንያት የፈተናውን

ምስጢር ለመጠበቅ እንዲቻል ነው፡፡ ፈተናው ለተፈታኞች ከመቅረቡ በፊትም በኮሚቴውና በድጓው መምህር በጥልቀት ይገመገማል፤ ይሻሻላል፡፡ የፈተናው ዓይነትም በዘመናዊዉ ትምህርት በዩኒቨርሲቲ በአብዛኛው የሚሠራበት ቡድን አወዳዳሪ (norm-referenced) ሳይሆን፣ መስፈርት-ተኮር (criterion-referenced) የሚባለው ነው፡፡ ፈተናው የሚዘጋጀው በታወቀ መስፈርት መሠረት ነው፡፡ ለአንድ ጊዜ የተሰጠ ፈተና ለሌላ ጊዜ የመግቢያ ፈተና አያገለግልም፡፡ በመስፈርቱ መሠረት በየጊዜው የሚዘጋጀው ፈተና አዲስ ነው፡፡ ጥያቄዎቹም ከየዘርፉ ዕውቀቶች (በተለይም ከዜማ ቤት) የሚዘጋጁ ኾነው በይዘትና በቅርጽ ዓይነተ ብዙ ናቸው፡፡[14] በመግቢያ ፈተናው የግለሰብ ብቃት እንጂ የቡድን ብቃት ወይም ችሎታ አይለካም፡፡ የመግቢያውን ፈተና ተፈትኖ ያለፈው አንድም ተማሪ ቢሆን ድጓ የማስመስከሪያ ትምህርት ይከታተላል፡፡ በቍጥር ደረጃ ሲታይ የመግቢያውን ፈተና እስካለፉ ድረስ፣ በአንድ ጊዜ የሚገቡት ተማሪዎች አንድም፣ ብዙም ሊኾኑ ይችላሉ፡፡ የድጓ ተማሪ ቅበላ በግል ችሎታ እንጂ በቍጥር አይወሰንም ማለት ነው፡፡ በዘመናዊዉ ትምህርት የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር እንደሚታወቀው ዐምስት ወይም ዐሥር ተማሪ ከሌለ መርሐ ግብሩ አይከፈትም፤ አይባልም፡፡

የመግቢያው ፈተና የሚካሄደው ዋናው የድጓ መምህር ባሉበት ነው፡፡ ተማሪዎች የመግቢያውን ፈተና የሚፈተኑት በተናጠልና በቃል ነው፡፡ በአንድ ጊዜ ሊፈተን የሚችለው አንድ ተማሪ ከኮሚቴው ፊት በአካል በመቅረብ ብቻ ነው፡፡ የመግቢያ ፈተና ለመፈተን የተመዘገቡት ኹሉም ተማሪዎች ተራቸውን ጠብቀው በዚሁ አግባብ በአካል እየቀረቡ ይፈተናሉ፡፡ ፈተናውን ተፈትኖ የጨረሰ ተማሪ ካልተፈተኑት ጋራ እንዲገናኝ አይፈቀድም፡፡ ይህን የሚከታተሉ የጥበቃ ሰዎች ይመደባሉ፡፡ ኹሉም ተማሪዎች ተፈትነው እስኪጨርሱ ድረስ የኮሚቴው አባላት ለማንኛውም ተግባር ከፈተናው አዳራሽ መውጣት አይፈቀድላቸውም፡፡ ምግብ ለመብላትም ቢሆን፣ ለመጸዳዳትም ቢሆን ከአዳራሽ መውጣት አይቻልም፡፡ ፈተናው እስከ ማታ ወይም እስከ ሌሊት ድረስ የሚቀጥል ቢሆንም ከአዳራሽ ሳይወጡ የመፈተን ተግባራቸውን የማከናወን ግዴታ አለባቸው (የቃለ መጠይቅ መረጃ)፡፡

ኹሉም ተማሪዎች መፈተናቸው ሲረጋገጥ ውጤት የሚነገረው ወዲያውኑ በዕለቱ ነው፡፡ ይህም የሚከናወነው ኹሉም ተፈታኞች በአካል ተገኝተው ነው፡፡ ሲፈተኑ በግል፣ ውጤት ሲያውቁ ግን በጋራ ይኾናል፡፡ አንድ ተማሪ ወደ ቅድስት ቤተ ልሔም የድጓ ማስመስከሪያ ትምህርት ቤት የሚገባው በመግቢያው ፈተና ቢያንስ ፳/፲ ወይም ፶/፻ ሲያስመዘግብ ብቻ ነው፡፡ እያንዳንዱ ተፈታኝ ስሕተቱን በራሱ ስለሚያውቅ በፈተናው ውጤት ላይ ቅሬታ የሚያቀርብ አይኖርም፡፡ በዚህ አግባብ የመግቢያውን ፈተና ያለፉት አድራሽ[15]፤ ተብለው፣ በጉባኤው ቋሚ ኮሚቴ ተመዝግበው ትምህርታቸውን ይቀጥላሉ፤ ያላለፉት ግን በሌላ ጊዜ ራሳቸውን

14 ከድጓ ስድስት፣ ከምዕራፍ አራት ጥያቄዎች ይካተታሉ (ሰላምሰው፣ 2017)፡፡
15 “ድጓ ለማስመስከር ቅድስት ቤተልሔም የድጓ ምስክር ትምህርት ቤት የሚገቡ ኹሉ አድራሽ ይባላሉ፤ ተማሪ አይባሉም፡፡” (ሀብተ ማርያም፣ 1963 ዓ.ም.፣ ገጽ፣ 99)፡፡

አዘጋጅተው እንደገና እንዲፈተኑ ምክር ይሰጣቸዋል፡፡ ከዚህም መረዳት የሚቻለው የድጓ ማስመስከር ትምህርት በፍላጎት ብቻ የሚገቡበት ሳይሆን፣ ሰፊና ጥልቅ ዕውቀት እንዲሁም ጠንካራ የግለ ብቃት እምነትና ቁርጠኛ መኾንን የሚጠይቅ መኾኑን ነው (ሽሊሜ፣ 1992)፡፡

በቅድስት ቤተ ልሔም የድጓ ምስክር ትምህርት ቤት የራሱ የኾነ ልዩ አስተዳደራዊ መዋቅርም እንዳለው ከምልከታና ከቃለ መጠይቅ መረጃዎች ተገንዝበናል፡፡ የድጓው ምስክር ትምህርት ቤት አስተዳደራዊና አካዳሚያዊ በሚል በኹለት ይከፈላል፡፡ አስተዳደራዊ ዘርፉ የሚመራው በራሳቸው በተማሪዎቹ ነው፡፡ ኹሉም የድጓ አስመስካሪ ተማሪዎች በአንድ ላይ ተሰብስበው ከመካከላቸው አስተዳዳሪ ወይም የተማሪዎች አስተዳዳር ሥራ እንዲሠራ ተስማምተው አንድ ተማሪ ይመርጣሉ፡፡ ይህ ተማሪ የተማሪዎችን አስተዳደራዊ ጉዳዮች በሚመለከት ሙሉ ሥልጣን አለው፡፡ አንድ ተማሪ ለምሳሌ፣ ትምህርቱን ጠንቅቆ ቢጨርስ እንኳ የድጓውን ምስክር ለማግኘት የተማሪዎች አስተዳዳሪ ምስክርነት ወይም ይሁንታ ያስፈልገዋል፡፡ የሥነ ምግባር ወይም ሌላ ችግር እንዳለበት በተማሪዎች አስተዳዳሪ የተመሰከረበት ተማሪ የምስክሩ ማኅተም አይመታለትም፡፡

በአካል ተገኝተን እንደታዘብነው ተማሪዎቹ የሚማሩበት አዳራሽና የመኖሪያ አካባቢያቸው ንጹሕ ናቸው፡፡ ተማሪዎቹም እጅግ ትሑትና ንጹሕ ናቸው፡፡ አዲስ ተማሪዎችን ወይም ሌላ እንግዳ በፍቅር የመቀበልና የማስተናገድ ሥርዐታቸውም እጅግ የሚገርም ነው፡፡ እጅግ ከፍተኛ ራስን የመምራትና የመማር ትጋት እንዳላቸውም አስተውለናል፡፡ ዓላማችሁ ምንድን ነው? በሚል ስንጠይቃቸው፣ መልሳቸው አንድ ነው፤ ድጓ ማስመስከር (academic excellence)፡፡ ይህ አስተሳሰብ ከትምህርቱ ወይም ከዕውቀቱ ይልቅ ቅጥርን ወይም ሥራ መያዝን ከሚያስቀድመው ከዘመናዊዉ የዩኒቨርሲቲ ትምህርት ባህል የሚቃረን መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

በቅድስት ቤተ ልሔም የድጓ ማስመስከሪያ ትምህርት ቤት የአካዳሚክ ዘርፉ የሚመራው ደግሞ በአንድ ሰው፣ በድጓው መምህር ነው፤ በሌላ አገላለጽ አካዳሚክ አስተዳደሩና የመማር-ማስተማሩ ሂደት የሚመራው በአንድ ሰው ነው፡፡ ቦታው የሚያዘው በሹመት ሳይሆን በውድድር ነው፡፡ የድጓ ምስክር ማኅተም ወይም የድጓ ዲግሪ ሊባል ይችላል፤ ዋናው መስፈርት ነው፡፡ በሌሎችም ተጨማሪ መስፈርቶች ከተወዳዳሪዎች መካከል ልቀው ለተገኙት የድጓ መምህር፣ በድጓ መምህር (መሪጌታ) ማዕረግ በኢ.ኦ.ተ.ቤ. ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት ቦታው (ወንበሩ) ይጸድቅላቸዋል፡፡ መሪጌታው በሞት ካልተለዩ ወይም በጤና እክል ምክንያት መሥራት ካልቻሉ ቦታውን (ወንበሩን) እንደያዙ ይቆያሉ፤ ከግራኝ አሕመድ ጦርነት በኋላ (እ.አ.አ. ፲፭፻፵፫) አስካሁን ድረስ የቅድስት ቤተ ልሔምን የድጓ ምስክር ትምህርት ቤት ፲፫ መሪጌታዎች መርተው አልፈዋል፡፡ የመጀመሪያው ዋናውን

መጽሐፈ ድጓ በዋሻ ደብቀው ከጉዳት ያተረፉት ሊቅ ልሳነ ዕፍረት[16]፣ ፲፫ኛው ሊቀ ምሁራን ሙሉ ገላው ሲሆኑ[17]፣ የአሁኑ ፲፬ኛው ደግሞ መሪጌታ ይትባረክ ከሳየ ናቸው። የመሪጌታው ሥራዎች በተማሪዎች ቊጥር የሚወሰኑ አይደሉም። የተማሪዎች ቊጥር ቢቀንስም፣ ቢጨምርም ሥራዎቹ የሚመሩት በአንድ ሰው ነው። ሥራዎቹ ተመሳሳይ ቢሆኑም በዘመናዊዉ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም እንደሚታወቀው የትምህርት ክፍል ተጠሪ፣ የፋኩልቲ ምክትልና ዋና ዲን፣ የድኅረምረቃ ዲን፣ የአካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዝዳንት ወዘተ. የመሳሰሉት ውስበብስብ ቢሮክራቲክ መዋቅሮች ለቅድስት ቤተ ልሔም የድጓ ምስክር ትምህርት ቤት አላስፈለጉም።

## መማር-ማስተማር

በቦታው ተገኝተን እንዳስተዋልነው በአሁኑ ጊዜ በቅድስት ቤተ ልሔም የድጓ ማስመስከር ትምህርቱ የሚካሄደው በአዳራሽ ውስጥ ነው፤ የጉባኤ አዳራሽ ይባላል። አዳራሽ ማለት ግን ምቹ ወንበርና ጠረጴዛ ያለው ወይም የተማሪዎች መቀመጫ ዴስክ ያለው ማለት አይደለም። ወደ አዳራሹ ሲገባ ከፊት ለፊት ካለው ግድግዳ አማካይ ጥግ ላይ ከፍ ብሎ ከተሠራ መለስተኛ መድረክ (stage) ላይ አንድ ወንበር አለ፤ የድጓው መምህር መቀመጫ ነው። በግራ በኩል ባለው ግድግዳ ጥግ ላይ ደግሞ በተመሳሳይ መጠን በተሠራ መድረክ ላይ ተጣጣፊ የድጓ ማስቀመጫ አትሮንስ ይገኛል። የድጓ ትምህርት ለመከታተል ተማሪዎች የየራሳቸውን ድጓና በብረት እግሮች ከገመድ ጥልፍልፍ የተሠራች አጭር በርጩማ ወንበር (stool) ይዘው ወደ አዳራሹ ይገባሉ። በርጩማዋ መቀመጫ፣ ጉልበታቸው ደግሞ የየግል ድጓቸው ማስደገፊያ ኾነው ያገለግላሉ። ዋናው ማስተማሪያ መጽሐፈ ድጓ (የምስክሩ ድጓ) ከመምህሩ ጋራ ወደ አዳራሽ ይገባል። ተረኛው አድራሽ ተማሪ ኩታ ለብሶ፣ ሻሽ ጠምጥሞ፣ ጭራ፣ አትሮንስና መጽሐፈ ድጓውን ይዞ ይመጣል። መምህሩ በሌሉበት ድጓው አይኖርም ማለት ነው። የምስክሩ ድጓ[18] የመጀመሪያው ቅጂ ስለኾነ ልዩ ጥበቃ ይደረግለታል። በዕለቱ ተረኛው አድራሽ ተማሪ ዋናውን ድጓ ያዜማል ወይም ያሄዳል (ትምህርቱ በተማሪ የሚጀመር መሆኑን ልብ ይሏል።)። እያንዳንዱ ተማሪ የየራሱን ድጓ ይዞ ያርማል፤ ይከታተላል። ስሕተት ሲኖር በመጀመሪያ ከተማሪዎች አንዱ ኹለት ጣቶቹን በማፋተግ ድምፅ በማሰማት ያስቆመውና ይጠይቀዋል። አድራሹ ተማሪ የራሱን መልስ ይመልሳል። መምህር በጽሞና


---

16 በ፲፯ኛው ክፍለ ዘመን በነበረው የግራኝ ጦርነት የቤተ ክርስቲያንና ቅርሶቿ ውድመት ምክንያት የድጓ ማስመስከሪያ ማእከል ከሆነችው ከቅደስት ቤተ ልሔም ውጭ ድጓ በሌላ ቦታ አልተገኘም (ቼሎት፣ 2002)።

17 ከ፪ኛው እስከ ፲፫ኛው የነበሩት በቅደም ተከተል፤ "(፪) መመህር ዘቃለ አብ፣ (፫) እጨጌ ቃለ ዓዋዲ፣ (፬) መምህር ተጠምቀ መድኅን፣ (፭) መምህር ሕንጸ ሃይማኖት፣ (፮) መምህር ወልደ መለኮት፣ (፯) መምህር ሠርፀ ማርያም፣ (፰) መምህር ክንፈ ሚካኤል፣ (፱) መምህር ገብረ እግዚአብሔር፣ (፲) አለቃ መርሻ፣ (፲፩) አለቃ አምሳሉና (፲፪) ሊቀ ምሁራን ጥበቡ ናቸው።" (ገሪማና ሌሎች፣ 2009 ዓ.ም.፣ ገጽ 118)።

18 ወጥነቱን ጠብቆ የኖረ፣ በማንም ያልተከለሰና ያልተበረዘ፣ በኢ.ኦተ.ቤ. ከፍተኛ ተመራማሪዎች ለጥናት ሥራ ካልሆነ በስተቀር ለማንም ተደራሽ የማይሆን ነው (ታደሰ፣ 1985)።

እያዳመጡ ማስተካከያ (እርማት) ይሰጣሉ፤ መምህር እያዜሙ ማስተካከያ የሚሰጡት ድጓውን ሳይመለከቱ ነው፤ ለመመልከት ቢፈልጉ እንኳን መጽሐፈ ድጓው ካጠገባቸው የለም፤ ሩቅ ነው። ለድጓ መምህር ድጓውን እየተመለከቱ ማዜም እንደ ደካማ መምህር ያስቆጥራል። ስለኾነም መሪጌታው በቃላቸው ነው እያዜሙ ማስተካከያ የሚሰጡት፤ ድጓውን ተክነውታል፤ ክልብ ነው የሚቆጣጠሩት (ሽሊሜ፣ 1992)። ከተማሪዎችም ጥያቄ ሲኖር እንደየሁኔታው በአድራሹ ተማሪ ወይም በመሪጌታው ይስተናገዳል። የማስተማሪያ ዘዴው ቀጥሎ ባለው ምስል እንደተመለከተው አንድ ለአንድና አንድ ለብዙ ዓይነት ሦስት ጎንዮሽ (triadic) መስተጋብር ያለው ነው።




አንድ ለአንድ ማለት የድጓ መምህሩና የድጓ አድራሹ ተማሪ መስተጋብር ሲሆን፣ አንድ ለብዙ ማለት ደግሞ አንድም በድጓ አድራሹ ተረኛ ተማሪና በእያንዳንዱ ተማሪ (መላው ተማሪዎች)፣ ኹለትም በድጓው መምህርና በሌሎች በመላው ተማሪዎች መካከል ያለው መስተጋብር ነው። ተረኛው የድጓ አድራሽ ተማሪ ድጓውን ሲያዜም አንድም ለመማር፣ ኹለትም ለማስተማር ነው። ተማሪው እየሠራ (እያዜመ) ከመምህሩ ይማራል። ሌሎቹ ተማሪዎች ደግሞ ከተማሪውና ከመምህሩ ይማራሉ ማለት ነው። ኹሉም ተማሪዎች በየተራቸው መሠረት አድራሽ ይሆናሉ (በቅድስት ቤተ ልሔም የድጓ ምስክር ትምህርት ቤት አድራሽ የማይሆን የድጓ ተማሪ አይኖርም።)፤ ይማራሉም፤ ያስተምራሉም ማለት ነው። እንዲህ ዓይነቱ በአድራሽ ተማሪ፣ በመምህርና በመላው ተማሪዎች መካከል ያለው ሦስት ጎንዮሽ መስተጋብር በቢኒስ (2005) እንደተገለጸው የድጓ ማስመስከር ሥርዐተትምህርት እምብርት ነው፤ ዘዴው እጅግ ሲበዛ ተማሪ አሳታፊ ነው።

የተግባር ልምምድ (internship) ደግሞ ሌላው የመማሪያ መንገድ ነው፤ ተማሪዎቹ ቅድስት ቤተ ልሔም ቤተ ክርስቲያንን እያገለገሉ በተግባር ይማራሉ። ራሳቸው እየተሳተፉ የሊቃውንቱን ምክርና አስተያየት ይቀበላሉ፤ የሊቃውንቱን አቅርቦትም በአንክሮ በማስተዋል ይማራሉ። ትምህርቱ የሚሰጠው ከሰኞ እስከ ዐርብ ከጧቱ ኹለት ሰዐት እስከ ቀኑ ስደስት ሰዐት ነው። ትምህርቱ ወይም ወንበሩ እንዳበቃ

መምህሩ ወደ ቤታቸው ሲሄዱ፣ ኹሉም ተማሪዎች ከጉባኤ አዳራሹ ሳይወጡ ባሉበት ኾነው በዕለቱ የተማሩትን ይቀጽላሉ (ይከልሳሉ)፡፡ ቅጸላው እንዳበቃ ስም ይጠራል፤ ከወንበሩ (ከጉባኤው) ያልተገኘ አድራሽ ተማሪ ይቀጣል፡፡ በተደጋጋሚ ያልተገኘ ሲሆን ደግሞ ከቅድስት ቤተ ልሔም የድጓ ምስክር ትምህርት ቤት ሊባረር ይችላል፡፡ ቅጸላው ካበቃ በኋላ ኹሉም ተማሪዎች ወደየጎጇቸው ይሄዱና ምሳቸውን ይበላሉ፡፡ ማታ፣ ማታ ወንበር ወይም ጉባኤ ስለማይኖር ኹሉም ተማሪዎች በጋራ ይቀጽላሉ፡፡

በቅድስት ቤተ ልሔም የድጓ ማስመስከር ትምህርት የሚከታተሉት ተማሪዎች በቆይታቸው ራሳቸውን በራሳቸው ነው የሚመሩት፤ ቀለባቸውንና የትምህርት መሣሪያዎችን የሚያሟሉት በራሳቸው ነው፤ ራስ አገዝ (self-sponsored) ናቸው፡፡ ለግል ወይም ለጋራ መኖሪያ የምትሆን ጎጆ ይሠራሉ፡፡ ቀለባቸው ሥንቅ ነው፡፡ ድጓ የማስመስከር ሕልም ያላቸው ቀደም ሲል በተማሩት ትምህርት ተቀጥረው ሲያገለግሉ ለዚሁ ዓላማ ብር ይቆጥባሉ፡፡ ከየአካባቢያቸው ሲመጡ ለተወሰነ ጊዜ የሚያቆያቸውን ሥንቅ (ልዩ ልዩ ዱቀት፣ ልዩ ልዩ ጥራጥሬ፣ ሽሮ፣ በርበሬ፣ ኮቸሮ፣ ቆሎ፣ ጨው ወዘተ. ማለት ነው፡፡) ቋጥረው ይዘው ይመጣሉ፤ የየዕለቱን ምግባቸውን ከሥንቃቸው እየቀነሱ ያዘጋጃሉ፡፡ ትምህርቱን ለመከታተልም የድጓ መጻፊያ ወረቀት (ለየት ያለ ነው፡፡)፣ በራሳቸው ድጓ የሚጽፉት ቀለምና መጻፊያ ብርዕ[19] እንዲኖሯቸው ያስፈልጋል፡፡ ወረቀቱን ይገዛሉ፤ መጻፊያ ቀለምና ብርዕ ግን ራሳቸው ነው የሚያዘጋጁት፡፡ ከተለያዩ ዕፀዋት የተለያዩ ቀለሞች (በአብዛኛው ጥቁርና ቀይ)፤ መጻፊ ብርዕ ከሸንበቆ ያዘጋጃሉ፡፡ በአሁኑ ጊዜ በማተሚያ ቤት ያለምልክት የታተመውን ድጓ ገዝተው ለሚጠቀሙት ግን መጻፊያ ቀለምና ብርዕ ብቻ ስለሚያስፈልጋቸው እነሱን በዚሁ አግባብ ያዘጋጃሉ፡፡

**የተማሪ ምረቃ**

ተማሪዎቹ የድጓ ማስመስከሪያ ትምህርቱን ለመከታተል የመግቢያ ፈተናውን ተፈትነው ሲያልፉ[20] ብቻ ትምህርታቸውን እንደሚቀጥሉት ኹሉ፣ ትምህርቱን ሲያጠናቅቁም ተፈትነው ግላዊ ብቃታቸው ይረጋገጣል፤ ፈተናውም በጋራ ሳይሆን በተናጠል ወይም በግል ነው፡፡ እንደ መግቢያው ፈተና ኹሉ የመመረቂያውም (የመውጫ) ፈተና መስፈርት-ተኮር ነው፡፡ በ፲፫ኛው የቅድስት ቤተ ልሔም የድጓ ምስክር ትምህርት ቤት መሪጌታ (ሊቀ ምሁራን) ሙሉ ገላው (1994 ዓ.ም.) ቃለ መጠይቅ መረጃ መሠረት፣ በቅድስት ቤተ ልሔም በድጓ ማስመስከር ለመመረቅ ሕጉ የሚፈቅደው ኹለት ዓመት ተኩል ነው፡፡ ሆኖም ድጓን በሌላ ቦታ በሚገባ አጥንቶና ጠንቅቆ ዐውቆ ለሚመጣ ጎበዝ ተማሪ በቅድስት ቤተ ልሔም ቆይታ

---

[19] "ሸንበቆ፣ የጎሽ መቃ፣ የሸንበቆ ዐይነት፣ ውስጥ ክፍት አገዳ ቅልጥም፡፡ በቁሙ የጸሓፊ ብር፤" (ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፤ *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ፣ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ*፡)፡፡ ይህም ትክክል ስለመሆኑ የዚህ ጥናት አንደኛው ገምጋሚ፣ ብዕር፤ የሚለው በስሕተት የተለመደው ቃል ፍቺ በሬ ማለት መሆኑን አስረጂ በማቅረብ መስክረዋል፡፡

20 ድጓ ለማስመስከር የቃል ፈተናውን ማለፍ አንደኛው አይቀሬ ግዴታ ነው (ቹሎት፣ 2002)፡፡

ተምሮ ለመመረቅ ኹለት ዓመት ሊወስድበት ይችላል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ድጓ በዓመት አንድ ጊዜ ስለሚዘለቅ፣ ተማሪው ጎበዝ ከኾነ በኹለት ዓመት ስለሚዘልቀው ነው፡፡ ለአንዳንዶቹ ግን የድጓ ማስመስከር ትምህርት እስከ ሰባት ዓመት ሊወስድባቸው ይችላል፡፡ ተማሪዎች ለፈተና የሚቀርቡት በራሳቸው ፈቃድና ጥያቄ ነው (ሰላምሰው፣ 2017)፡፡ አንድ ተማሪ በራሱ ተነሣሽነት ለመፈተን ጥያቄ ሲያቀርብ፣ ፈተናውን የሚፈተነው በሊቃውንቱ መካከል በተራ ወንበር[21] ላይ ነው፡፡ በዚህ አግባብ አንድ ተማሪ ተራ ወንበር ተሰጥቶት ለመፈተን ከተማሪዎቹ ቍጥር ብዛት የተነሣ ከሦስት እስከ አራት ወራት ድረስ ተራ ሊጠብቅ ይችላል፡፡ ተራው ደርሶት ተፈትኖ ያላለፈ ተማሪ እንደገና አጥንቶና አሻሽሎ በሌላ ተራ ተመልሶ እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡

በድጓ ማስመስከር ትምህርት ፈተናውን ማለፍ ብቻውን ግን ለምረቃ አያበቃም፡፡ ግርማ (1967) እንደሚገልጸውና በቃለ መጠይቅም እንደተረጋገጠው፣ ከትምህርቱ ባሻገር እያንዳንዱ ተማሪ በመምህሩ አማካይነት እንደታማኝነትና ሐቀኛነት ባሉ ሌሎች የመልካም ባሕርይ/ሰብእና መለኪያዎች በተከታታይ ይመዘናል፡፡ ፈተናውን ያለፈና መልካም ሰብእናውም የተመሰከረለት ተማሪ ከቅድስት ቤተ ልሔም የድጓ ምስክር ትምህርት ቤት ሦስት የትምህርት ማስረጃዎች ይሰጡታል፤ አንደኛ ፈተናውን ተፈትኖ ያለፈ ተማሪ ለመመረቅ ያለምልክት በማተሚያ ቤት የታተመውን ድጓ አመልክቶ ጠንቅቆ አርሞ ያቀርባል፡፡ ይህም በሊቃውንቱ ተረጋግጦ ይሁንታ ሲያገኝ፣ በድጓው የመጀመሪያና የመጨረሻ ገጾች ጎዳግ ላይ ስለትክክለኛነቱ የምስክር መምህሩ ማኅተም ይደረግለታል፤ ኹለተኛ በቅድስት ቤተ ልሔም የድጓውን ትምህርት ተምሮ ስላጠናቀቀና ፈተናውንም ስላለፈ ወንበር ተክሎ ጉባኤ ዘርግቶ ማስተማር የሚችል መኾኑን የሚገልጽ "ቃለ በረከት" የሚባል ደብዳቤ ለመጣበት ደብር ይጻፍለታል፤ ሦስተኛ በማተሚያቤት ታትሞ የተዘጋጀ የምስክር ወረቀት ፎቶግራፉ ተደረጎበት በማኅተም ተረጋግጦ ይሰጠዋል፡፡

በተጨማሪም ለተመራቂው ተማሪ የምስክሩ መምህር የልብ ጸሎት ያደርጉለታል፤ የልብ ምርቃት ይመርቁታል፤ "መሪጌታ" ብለው ይሰይሙታል፡፡[22] የዚህም አንድምታ የድጓ መምህር እንዲሆን፣ እንዲያስተምርም ምስክር (ዲግሪ) ተሰጠው ማለት ነው፡፡ በዚህም የተነሣ ድጓውን አስመሰከረ ከመባል ይልቅ፣ አስመረቀ ይባላል፡፡ ሽግግሩ ከተማሪነት ወደ አድራሽነት፣ ከአድራሽነት ወደ መሪጌትነት ይሆናል፡፡ "መሪጌታ" ተብሎ ከተሰየመ በኋላ ተማሪዎች እንደ ንብ አውራ ይከቡታል፤ ያጅቡታል፡፡ እሱም ሳይውል ሳያድር አደራ የተጣለበት በመኾኑ ማስተማር ይጀምራል፡፡ በተማሪዎች መከበብና መታጀብ ሌላው የአዋቂነት/የሊቅነት ማስመስከሪያም ነው (ሀብተ ማርያም፣ 1963 ዓ.ም.)፡፡ ይህም በዘመናዊዉ የዩኒቨርሲቲ ትምህርት ምረቃ ከሚከናወነው ሥነ ሥርዐት ጋር ተመሳሳይነት እንዳለው ልብ ይሏል፡፡

---

21 “ወንበር ተክሎ ጉባኤ ዘርግቶ ለማስተማር አልተመረቀምና ባለወንበር አይደለም፡፡” (ሙሉ፣ 1994 ዓ.ም.፣ ገጽ 114)፡፡

22 በቅድስት ቤተ ልሔም የድጓ ምስክር ትምህርት ቤት በዓመት ሦስት ጊዜ የምረቃ ሥነ ሥርዐት ይከናወናል (ሰላምሰው፣ 2017)፡፡

ባጠቃላይ ከሂደቱ መረዳት እንደሚቻለው በቅድስት ቤተ ልሔም የድጓ ምስክር ትምህርት ቤት የራስን ብቸኛ ብቃት ማስመስከር እንጂ በማንኛውም ሁኔታ መኮረጅ ወይም መስረቅ (plagiarism) አይታሰብም፡፡ የድጓ ማስመስከር ዕውቀት ወይም ብቃት በግዥ ወይም በስርቆት አይገኝም ማለት ነው፡፡ ድጓውን በተራ ጠብቆ የዘለቀና ይትበሀሉን[23] ጠንቅቆ ያወቀ ተማሪ ብቻ እንዲያስተምር የምስክር ወረቀት (ዲግሪ) ይሰጠዋል፡፡ ጠንቅቆ አመልክቶ አርሞ በሚያቀርበው ድጓውም ላይ ስለትክክለኛነቱ ማኅተም ይታተምለታል፤ ለተወለደበት ወይም ለሚቀጠርበት ደብር ድብዳቤ ይጻፍለታል፡፡ ከዚህ ውጪ የሚታሰብ አልባሌ ወይም ተራ የማጭበርበር ባህል የለም፡፡

## ከቅደስት ቤተ ልሔም የድጓ ምስክር ትምህርት ቤት ዘመናዊዉ የኢትዮጵያ ትምህርት የሚማራቸው ብርቱ ቁምነገሮች

በኢትዮጵያ ዘመናዊ ትምህርት ሲጀመር ሥርዐተ ትምህርቱ በቀጥታ ከምዕራባውያን ሀገራት የተቀዳ በመሆኑ (ሞላና ሌሎች፣ 2022)፣ ነባሩ ጥንታዊ ትምህርትና ዘመናዊ ትምህርት ተዋሕደው ርስበርስ የሚጠቃቀሙበት እድል አላገኙም፡፡ ለዚህም ሰጣርገው (2004) እንደገለጸው ዘመናዊዉን ትምህርት ከጥንታዊዉ ትምህርት ጋራ ለማስተሳሰር ጥረት አለመደረጉ አንድ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ እንዲሁም ከውጭ የተቀዳው ዘመናዊዉ ትምህርት ከሀገራዊዉ ፍልስፍና፣ ባህል፣ ታሪክና ሥነ ልቡና የተነጠለና ዐውዳዊነት የጎደለው መሆኑ ተጨማሪ ምክንያት ይሆናል፡፡ በሌላ አገላለጽ ጥንታዊዉና ዘመናዊዉ ትምህርቶች ፍልስፍናዊ፣ ባህላዊ፣ ታሪካዊና ሥነ ልቡናዊ መሠረታቸውም የተለያየ ስለኾነ አንዳቸው ከሌላቸው ተጠቃሚ የሆኑበት አጋጣሚ እስካሁን ብዙም አልታየም፡፡ ተከሥተ (1996) እንደሚገልጸው በኢትዮጵያ ሀገር በቀል የኾነውና ሃይማኖታዊ መሠረት ያለው ጥንታዊዉና ዘመናዊዉ ትምህርት እንደባላንጣ/ደመኛ ሳይኾን እንደአጋዥ/አጋር ሊተያዩና ርስበርስ ሊጠቃቀሙ ይገባል፡፡ ለምሳሌ፣ የአብነት ትምህርት ቤቶች ለማኅበረሰቡ ቅርብና ተደራሽ በመሆናቸው በእነሱ አማካይነት መሠረታዊ ትምህርትን ማስፋፋት ይቻላል፡፡ በተጨማሪም በቼሎት (2009) እንደተገለጸው በጥንታዊዉና በዘመናዊዉ ትምህርቶች መካከል ውሕደትና መተጋገዝ በመፍጠር በተለይም የጥንታዊዉን ትምህርት ከመጥፋት መታደግ ይቻላል፡፡ የአብነት ትምህርት ቤት ዳራ ያላቸው የዘመናዊ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ልዩ የማስታወስ ብቃትና መልካም ሥነ ምግባር እንዳላቸው ያረጋገጡ ጥናቶች አሉ (ቢኒስ፣ 2005)፡፡ ስለኾነም በጥንታዊዉ ትምህርት ለትውልድ ሲተላለፉ ተጠብቀው የቆዩትን ጠቃሚ የዕውቀትና የባህል ሀብቶች በአግባቡ መርምሮና ገምግሞ በዘመናዊዉ የትምህርት ሥርዐት ውስጥ ማካተት እጅግ በጣም ተጠቃሚ ያደርጋል፡፡

23 "ይትበሀል ማለት በዚህ ጊዜ ይኽ ይባላል፤ እንደማለት ነው፤ ሥነ ሥርዓት ማለትም ይሆናል፤ የቤተ ክርሲቲያን ሥነ ሥርዓት አንድም በዚያን ጊዜ ይኽ ይባል ብላ የወሰነችው ሕግ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በድጓው ይትበሀል መሠረት ስለሚከናወን ይህንኑ ጠንቅቆ ማወቅና መከተል ይገባል፡፡" (ሀብተ ማርያም፣ 1963 ዓ.ም.፤ ገጽ፣ 88-89)፡፡

በዚህ ጥናት ለማሳየት እንደተሞከረው ጥንታዊነቱን ጠብቆ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ ከመጣው፣ ከቅድስት ቤተ ልሔም የድጓ ምስክር ትምህርት፣ ዘመናዊዉ የኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዐት የሚማራቸው ሥነ ትምህርታዊ፣ ሥነ ምግባራዊ፣ አስተሳሰባዊና አስተዳደራዊ ብርቱ ቁምነገሮች የሚከተሉት ናቸው፡፡

**ሊቅነት** (intellect)፤ በጳውሎስ (1976) የተጣቀሱት የአውሮፓ ሚሽነሪዎች (ኤም ዲ ጃኮቢስ) በአብነት ትምህርት ሂደት ውስጥ የሚያልፉት የኢትዮጵያ ሊቃውንት በአውሮፓ ትምህርት ቤቶች ከተማሩት ፕሮፌሰሮች በላይ ሲበዛ ዐዋቂዎችና ሊቆች ናቸው፤ በሚል መስክረዋል፡፡ በስሜት ሳይሆን በዕውቀትና በተጠየቅ የሚመሩ ሊቆች ናቸው፤ ሲሉም መስክረዋል፡፡ በቅርጹና በይዘቱ ረቂቅ፣ በቃለ ኃይሉ ታላቅ የኾነውን መጽሐፈ ድጓ ከልብ ተቆጣጥረው የሚያስተምሩ መሪጌታዎች፣ በዚሁ አግባብ ብቃታቸው ተረጋግጦ ተመርቀው የሚወጡ ተማሪዎች በርግጥም ሊቆች ናቸው፡፡

***ሀገር በቀል ዕውቀት***፤ ***በሀገር በቀል ቋንቋና በሀገር በቀል መማሪያ ማስተማሪያ ዘዴ***፤ ድጓ ሲወሣ አብሮ የሚወሣው ኢትዮጵያዊው ታላቅ ሊቅ ደራሲ፣ ገጣሚ፣ ባለቅኔና የዜማ አባት ቅዱስ ያሬድ ነው፡፡ የድጓ ዕውቀት ሀገር በቀል ነው፤ የሚባለውም በኢትዮጵያዊዉ ሊቅ ኢትዮጵያ ውስጥ ተፈጥሮ ያደገና የተስፋፋ በመሆኑ ነው፡፡ እንደ ሃይደንና ሞዛርት የተሰኙት ስመጥር የአውሮፓ የሙዚቃ ሊቃውንት የመጡት ቅዱስ ያሬድ ሦስቱን የዜማ ዓይነቶች (ግእዝ፣ ዕዝልና አራራይ) እና ስምንቱን የዜማ ምልክቶች ፈጥሮ ካስተዋወቀ ከ፲፪ ዓመት[24] በኋላ ነው፡፡ መጽሐፈ ድጓው የተደረሰው በሀገር በቀሉ ቋንቋ በግእዝ ነው፤ የአድራሽ ተማሪን፣ የድጓ መምህሩንና የመላው ተማሪዎችን ሦስት ጎንዮሽ መስተጋበር የሚያሳየው የድጓ መማር-ማስተማር ዘዴም ከጥንት ጀምሮ ከመሪጌታ ወደ መሪጌታ ሲተላለፍ የኖረና አሁንም ያለ ሀገር በቀል የመማሪያና ማስተማሪያ ዘዴ ነው፡፡

***የሞራል ልዕልና፣ መልካም ሥነ ምግባር፣ ሀገር ወዳድነት፣ ትሕትና፣ ታማኝነት፣ ሐቀኛነት***፤ በቅድስት ቤተ ልሔም የድጓ ማስመስከር ትምህርት የሚከታተሉ ተማሪዎች ከድጓ ማስመስከር በተጨማሪ በቆይታቸው የሚገነቧቸው የሞራል ልዕልና፣ የመልካም ሥነ ምግባር፣ የሀገር ወዳድነት፣ የትሕትና፣ የታማኝነትና የሐቀኛነት ዕሴቶች ትልቅ ዋጋ ያላቸው ናቸው፡፡ እነዚህን መልካም ዕሴቶች የሚገነቧቸው ከመምህራቸውና ከርስበርስ በፍቅር የመኖርና የመማማር መስተጋብር ነው፡፡ የድጓው መምህር የወላጅ ሚና አላቸው፤ ለተማሪዎቻቸው አርኣያ ኾነው በማሳየትና በመምራት ተማሪዎቹ መንፈሰ ጠንካራ፣ ትሑት፣ ታማኝና ሐቀኛ እንዲሆኑ ጥረታቸው ከልብ ነው (ግርማ፣ 1967)፡፡ ተማሪዎቹ እነዚህን መልካም ዕሴቶች የሚማሯቸው በድርጊት በመፈጸም ነው፡፡ የአዳዲስ ተማሪዎች ወይም ሌሎች እንግዶች አቀባበልና መስተንግዶ ሥርዐት አንዱ የሞራል መገንቢያቸው መንገድ ነው፤ እንግዶችን በፍቅር ይቀበላሉ፤ ያስተናግዳሉ፤ ይመግባሉ፤ እግር ያጥባሉ፤ መኝታቸውን ለቀው (ዐልጋም ቢሆን) ያስተኛሉ፡፡ የእነዚህ ጠቃሚ ዕሴቶች

24 (https://allaboutethio.com/books/libraryee55.pdf)

ባለቤት የሆኑ ምሩቃን ሞራላዊና ሥነ ምግባራዊ ያልሆኑ ድርጊቶችን በመጠየፍ ሀገራቸውንና ሕዝባቸውን በፍቅር ማገልገል ስለመቻላቸው የሚያጠራጥር አይሆንም፤ ተማሪዎቹ ድጓ አስመስክረው የሚመረቁት ራሳቸውን ብቻ ሳይሆን ማኅበረሰባቸውን በቅንነት፣ በታማኝነትና በሐቅ የማገልገል ብቃታቸው ጭምር ተረጋግጦ ነው፡፡

**ጠንካራ የመማር ትጋት/ተነሣሽነት**፤ ተማሪዎች ጠንካራ የዓላማ ጽናት ስላላቸው የመማር ትጋታቸውም ከፍተኛ ነው፡፡ ስለቅድስት ቤተ ልሔም የድጓ አስመስካሪ ተማሪዎች ጽናት፣ ሙሉ ገላው (1994 ዓ.ም.፤ ገጽ 116)፤ "ተማሪዎች የመጡበት ሥራቸው ዓላማቸው ስለኾነ ምንም ዓይነት ችግር ቢያጋጥማቸው የከፋ ረኃብም ቢሆን ችግሩን ተቋቁመው በጽናትና በትዕግሥት ይማራሉ እንጂ ትምህርታቸውን አቋርጠው ወደየመጡበት እስከመሄድ የደረሱ ተማሪዎች እስካሁን የሉም፡፡" ብለዋል፡፡ በዚህ ጥናትም በምልከታና በቃለ መጠይቅም እንደተረጋገጠው ተማሪዎቹ የሚማሩት በምቾት አይደለም፤ መማሪያቸው፣ ማደሪያቸውና ቀለባቸው ኹሉ ምቾት ያለው አይደለም፡፡ ኾኖም ጠንካራ የዓላማ ጽናት ስላላቸው ማንኛውንም ችግር ተቋቁመው ትምህርታቸውን በጽናት ይከታተላሉ፤ ብቃታቸውንም አስመስክረው ለስኬት ይበቃሉ፡፡

**ትብብራዊ መማር**፤ በድጓ ማስመስከር ትምህርት ትብብራዊ የመማር ዘዴ በጉባኤ ላይና ከጉባኤ ውጭ ይተገበራል፡፡ ይህም እኩል ተሳትፎ፣ የጋራ ግብና የግል ኃላፊነት ያለው ነው፡፡ በድጓ ማስመስከር ትምህርት የኹሉም ተማሪዎች የጋራ ግብ ድጓ ማስመስከር ነው፡፡ ስለኾነም ኹሉም ተማሪዎች በአድራሽነት ሚና እኩል ተሳትፎ አላቸው፡፡ በዚህም ኹሉም የመማርና የማስተማር ግላዊ ኃላፊነታቸውን በትክክል ይወጣሉ፡፡ ከጉባኤ ውጭም በጥንድ ወይም በቡድን እየኾኑ በእኩል ተሳትፎና በግል ኃላፊነት ለጋራ ግብ በትብብር የሚማሩባቸው አጋጣሚዎች እጅግ በርካታ ናቸው፡፡

**በራስ ፍጥነት መማር** (self-paced learning)፤ ተማሪዎች በተመሳሳይ ወይም በተለያየ ጊዜ በግል ወይም በቡድን የድጓ ማስመስከር ትምህርት ለመማር ወደ ቅድስት ቤተ ልሔም ሊገቡ ይችላሉ፡፡ ሆኖም በቅድስት ቤተ ልሔም የድጓ ምስክር ትምህርት ቤት እንደዘመናዊ ዩኒቨርሲቲ ዐብሮ ገብ የሚባል ሥርዐት የለም፡፡ አዳዲስ ተማሪዎች ሲገቡ ቊጥራቸው ቢያንስም፣ ቢበዛም ነባሮቹ ከደረሱበት ነው ትምህርቱን የሚጀምሩት፡፡ ይህም የሚኾነው ያልተማሩትን ዙረው ስለሚደርሱበት ነው፡፡ በዚህም ኹሉም ተማሪዎች እንደየራሳቸው ፍጥነት ነው የሚማሩት፤ ፈጣን የሆኑት ከሌሎቹ ቀድመው ሊጨርሱ ይችላሉ፤ መጠባበቅ የለም፤ ዐብሮ ገብን ጠብቆ በአንድ ላይ መመረቅ፤ የሚባል ነገር የለም፤ ይህም በቅድስት ቤተ ልሔም የተፈቀደ ነው፡፡ ፈጣን ተማሪዎች ኹለት ዓመት ከተማሩ በኋላ ለመመረቂያ ፈተና ሊያመለክቱ ይችላሉ፤ ተፈትነው ካለፉ ተመርቀው ወይም ድጓ አስመስክረው ይወጣሉ፡፡

**መሰፈርት-ተኮር ምዘና**፤ በጥናቱ እንደተብራራው የድጓ አስመስካሪ ተማሪዎች ቅበላና ምረቃ በመሰፈርት-ተኮር ምዘና ላይ የተመሠረተ ነው። ተማሪዎቹ ለመማር ሲገቡም ኾነ ትምህርታቸውን አጠናቀው ሲወጡ ግላዊ ችሎታቸው ወይም ብቃታቸው በመስፈርት-ተኮር ምዘና ይረጋገጣል። የመግቢያ ፈተናው በታወቀ መስፈርት ላይ ተመሥርቶ የግለሰብን ብቃት ብቻ ስለሚለካ ለመግባት ወይም ላለመግባት የሚያስችል ብቸኛ መለኪያ ነው። የመውጫ ወይም ለምረቃ የሚያበቃው ፈተናም በተመሳሳይ ሁኔታ የግል ብቃትን ለማስመስከር መቻል አለመቻልን ይለካል። የግል ብቃት ሳይረጋገጥና ሳይመሰከር ዘሎ መግባትም፣ መውጣትም አይቻልም።

**ተተኪ መፍጠር/የተማሩትን መጠቀም/ማስተማር** (emulation)፤ ድጓ ያስመሰከሩ መሪጌታዎች (በሌሎችም የአብነት ትምህርት ዘርፎች እንዲሁ) ሙያቸውንና ዕውቀታቸውን ለተተኪዎቻቸውና ለመጭው ትውልድ የማስተላለፍ ሞራላዊና ሃይማኖታዊ ግዴታ አለባቸው። ለዚህም ነው የድጓ ትምህርት ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የኖረው። በቅድስት ቤተ ልሔም የድጓ ምስክር ትምህርት ቤት ድጓ አስመስክረው የተመረቁ ተማሪዎች የተማሩትን ኹሉ በብቃት ይጠቀማሉ፤ እንደተማሩት አድርገው ይተገብራሉም። ያለፉባቸው የትምህርት ሂደቶች የተማሩትን እንዲያስተምሩ ብሎም ተተኪ እንዲፈጥሩ ግድ ይሏቸዋል። እንደተማሩት አድርገው ያስተምራሉ፤ በሌላ አባባል በተማሩትና በሚያስተምሩት መካከል ልዩነት የለም ማለት ነው።

**ራስን መግዛት** (self-discipline) **እና በራስ መተማመን** (self-confidence)፤ የድጓ አስመስካሪ ተማሪዎች ራሳቸውን ያስገዙ ለሚያጋጥማቸው ችግር ኹሉ የማይበገሩ ራሳቸውን ለመልካም ሥነ ምግባር ያስገዙ መልካም ምግባርና በራስ መተማመን ያላቸው ናቸው። በዕውቀታቸው ብቻ ሳይሆን፣ በመልካም ምግባራቸው ለሌሎች አርኣያ የሚሆኑ ናቸው።

**ተማሪ አሳታፊ የትምህርት አስተዳደርና ምዘና**፤ በጥናቱ በግልጽ እንደተመለከተው በቅድስት ቤተ ልሔም የድጓ ማስመስከሪያ ትምህርት ቤት አስተዳደራዊ ዘርፉ በተማሪዎች፣ አካዳሚክ ዘርፉ ደግሞ በድጓ መምህር (መሪጌታ) ይመራል። ተማሪዎች በአስተዳደራዊ ሥራው በመሳተፋቸው ኃላፊነት መውሰድንና ራስንና ሌሎችን የመምራት ክሂሎት ለማጎልበት ይረዳቸዋል። ተማሪዎች በአስተዳደር ሥራ ብቻ ሳይሆን በድጓ ማስመስከር ትምህርት የተማሪ ቅበላ ምዘናም ላይ ይሳተፋሉ፤ በጥናቱ እንደተገለጸው የመግቢያ ፈተናውን በሚያዘጋጀው ኮሚቴ ውስጥ ነባር ተማሪዎች ይሳተፋሉ።

**የተግባር ልምምድ**፤ በድጓ ማስመክር ትምህርት በጉባኤ አዳራሽ ውስጥ የሚካሄደው ትምህርት በቅድስት ቤተልሔም ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በተግባር ልምምድ የሚደገፍ ነው፤ ኹሉም የድጓ አስመስካሪ ተማሪዎች በቅድስት ቤተ ልሔም የቤተ

ክርስቲያን የአገልግሎት ሥነ ሥርዐት ላይ በቀጥታ ተሳታፊ በመኾን ወይም ታዳሚ ኾኖ በንቃት በመከታተል የተግባር ልምምድ ያደርጋሉ።

**የግል ብቃትን ማስመስከር፤** ከቅድስት ቤተ ልሔም የድጓ ማስመስከሪያ ትምህርት ቤት ድጓ አስመስክረው የሚመረቁ ተማሪዎች የግል ብቃታቸው የተመሰከረላቸው ናቸው። ለዚህም ማስረጃ እንዲሆን (፩) ጠንቅቀው አርመውና አስተካክለው በሚያቀርቡት የግል ድጓቸው የመጀመሪያና የመጨራሻ ገጾች ኅዳግ ላይ ስለትክክለኛነቱ የምስክሩ መምህር ማኅተም ይደረግላቸዋል፤ (፪) ወንበር ዘርግተው ድጓ ማስተማር የሚችሉ መኾናቸውን የሚገልጽ የቃለ ቡራኬ ድብዳቤ ይጻፍላቸዋል፤ (፫) ፎቷቸው ያለበት በማተሚያ ቤት የታተመ የምስክር ወረቀት (ዲግሪ ሊባል ይችላል፤) ይሰጣቸዋል።

***ማጠቃለያ***

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በቅድስት ቤተ ልሔም ቤተ ክርስቲያን የድጓ ማስመስከር ትምህርትን በመመርመር ሥነ ትምህርታዊ ፋይዳውን ማሳየት ነበር። ጥናቱ የተከተለው ስልት ገላጭ ሲሆን፣ ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ፣ የተኖረ ተመክሮና ተዛማጅ ድርሳናት ዋና ዋና የመረጃ ምንጮች ናቸው። የጥናቱ ዋና ትኩረቶችም የተማሪ ቅበላና አስተዳደር፣ መማር-ማስተማርና ምረቃ ናቸው። የድጓ ማስመከር ትምህርት ለመከታተል ወደ ቅድስት ቤተ ልሔም የድጓ ምስክር ትምህርት ቤት ለመግባት የመግቢያ ፈተናውን ማለፍ የግድ ይሆናል። ይህም ማለት የድጓ ማስመስከር ትምህርት ለመከታተል በቀዳሚነት ከተማሪው የሚጠበቁ ተፈላጊ ብቃቶች አሉ ማለት ነው። የቅድስት ቤተ ልሔምን የመግቢያ ፈተና ልዩ የሚያደርገው በመስፈርት-ተኮር ፈተና የግል ብቃት የሚረጋገጥበት መኾኑ ነው። ፈተናው ከዝግጅቱ አስከአፈጻጸሙ ድረስ ግለብቃትን በትክክል መለካት እንዲችል ብርቱ ጥንቃቄ ይደረግለታል። በመሪጌታው የሚመረጡ ነባር ተማሪዎችና ሊቃውንት በፈተና አዘጋጅና ፈጻሚ ኮሚቴ ውስጥ ይሳተፋሉ። የመግቢያ ፈተናው ለተማሪዎች ከመቅረቡ በፊት በኮሚቴውና በመሪጌታው በጥልቀት ተገምግሞ ይሻሻላል። ተማሪዎች ፈተናውን የሚፈተኑት በግል በኮሚቴው ፊት በአካል እየቀረቡ በቃል ነው። የተፈታኞቹ ቍጥር ቢበዛም፣ ቢያንስም የመግቢያ ፈተናው የሚጠናቀቀውና ውጤትም የሚነገረው በዕለቱ ኹሉም ተፈታኞች ባሉበት ነው። የመገቢያውን ፈተና ያለፉት ተማሪዎች ለድጓ ማስመስከር ትምህርት ተመዝግበው ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ ሲፈቀድላቸው፣ ያላለፉት አሻሽለው በሌላ ጊዜ እንዲፈተኑ ይመከራሉ።

በቅድስት ቤተ ልሔም የድጓ ምስክር ትምህርት ቤት አስተዳደሩ ኹለት ዘርፎች አሉት። አስተዳደራዊና አካዳሚክ፤ የተሰኙ ኹለት መዋቅሮች አሉት። አስተዳደሩ በመላው ተማሪዎች ስምምነት በሚመረጥ አንድ ተማሪ (የተማሪዎች አስተዳዳሪ) ይመራል። በማንኛውም አስተዳደራዊ ጉዳዮች የመወሰን ሙሉ ሥልጣን አለው። ይህም ተማሪዎች ከድጓው ትምህርታቸው በተጨማሪ ራስን በራስ የመምራትና

የማስተዳደር ዐቅም እንዲያጎለብቱ ዕድል ይሰጣል፡፡ የአካዳሚክ ዘርፉ ደግሞ በድጓው መምህር (መሪጌታ) ነው የሚመራው፡፡ የድጓው መምህር አካዳሚክ ጉዳዮችን በተመለከተ ከመነሻ እስከ መድረሻ ያስተዳድራሉ ማለት ነው፡፡

በቅድስት ቤተ ልሔም የድጓ ማስመስከሪያ ትምህርት ቤት የመማር-ማስተማሩ እንደዘመናዊዉ የዩኒቨርሰቲ ትምህርት የመምህርና የተማሪ መስተጋብር ያለው ቢሆንም፣ የራሱ ልዩ ባሕርያት ግን አሉት፡፡ የዘመናዊዉ ትምህርት የመምህር-ተማሪ መስተጋብር ኹለትዮሽ ኾኖ፣ መምህርን ከፊት ያስቀደመና ተማሪን ከኋላ ያስከተለ መምህር-መራሽ ነው፤ ትምህርት የሚጀመረው በመምህር ነው፡፡ በቅድስት ቤተ ልሔም የድጓ ምስክር ትምህርት ቤት ግን ከዚህ በተቃራኒው መስተጋብሩ ሦስት ጎንዩሽ ያለው ሲኾን፣ ተማሪ-መራሽ ነው፤ ለማለት ይቻላል፡፡ በሌላ አገላለጽ ትምህርቱ የሚጀመረው በተማሪ ነው ማለት ነው፡፡ በዚህ የሦስትዮሽ መስተጋብር ሦስት ተዋንያን ያሉ ሲኾን፣ እነሱም ተረኛ አድራሽ ተማሪ፣ የድጓው መምህርና መላው ተማሪዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ሦስቱ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ሦስት ጎንዮሽ መስተጋብር ይፈጥራሉ፡፡ ተረኛ አድራሽ ተማሪው ዋናውን ድጓ እያዜመ ትምህርቱን ይጀምራል፡፡ መምህር በጽሞና እያዳመጡ ያርማሉ፡፡ መላው ተማሪዎች ከአድራሽ ተማሪውና ከመምህሩ እየተከታተሉ የግል ድጓቸውን ያመለክታሉ፤ ያርማሉ፡፡ ጥያቄ ሲኖራቸው ይጠይቃሉ፡፡ በዚህ አግባብ ተማሪዎች በጉባኤ አዳራሽ ውስጥና ከጉባኤ አዳራሽ ውጪ ለጋራ ግብ ግላዊ ኃላፊነታቸውን እየተወጡ በትብብር ይማራሉ፡፡ መማር-ማስተማሩ በተግባር ልምምድም የታገዘ ነው፡፡

የድጓ ማስመስከር ትምህርት ለመከታተል ወደ ቅድስት ቤተ ልሔም የሚገባው ተማሪ የመግቢያውን ፈተና ያለፈ ብቻ እንደኾነ ኹሉ፣ የሚመረቀውም (ድጓ የሚያስመሰክረው) የመውጫውን ወይም የማጠናቀቂያውን ፈተና ያለፈ ብቻ ነው፡፡ ድጓን ጠንቅቆ ዐውቆ ብቃትን ለማስመስከር በሊቃውንት መካከል በግል መፈተን ይጠበቃል፡፡ በዚህም የግል ብቃቱ በሊቃውንቱ የተመሰከረለት ተማሪ፣ (፩) ጠንቅቆ አመልክቶና አርሞ በሚያቀርበው በማተሚያ ቤት በታተመ ድጓ የመጀመሪያና የመጨረሻ ገጾች ጎዳግ ላይ የምስክር መምህሩ ማኅተም ይደረግለታል፤ (፪) ድጓ ተምሮ ማጠናቀቁን፣ ፈተናውን ማለፉንና ወንበር ዘርግቶ ማስተማር የሚችል መኾኑን የሚገልጽ የቃለ ቡራኬ ደብዳቤ ይጻፍለታል፤ (፫) ስሙ የተጻፈበትና ፎቶግራፉ ያለበት በማተሚያ ቤት የታተመ የምስክር ወረቀት (ዲግሪ) የምስክሩ ማኅተም ተደርጎበት ይሰጠዋል፡፡ በዚህም ከተራ ተማሪነት ወደ አድራሽነት፣ ከአድራሽነት ወደ መሪጌትነት ያለው ጉዞ ይቋጫል ማለት ነው፡፡

በቅድስት ቤተ ልሔም የድጓ ማስመስከር ትምህርት ሂደት ከቅበላ እስከ ምረቃ ድረስ ከላይ በተገለጸው አግባብ የሚከናወን ሲሆን፣ ከለዚህም ከታች እስከላይ ያሉት የዘመናዊ የኢትዮጵያ የትምህርት ተቋማት የሚማሯቸው ብርቱ ቁምነገሮች ተለይተዋል፡፡ እነሱም **ሊቅነት፣ ሀገር በቀል ዕውቀት፤ በሀገር በቀል ቋንቋና በሀገር በቀል መማሪያ-ማስተማሪያ ዘዴ፤ የሞራል ልዕልና፣ ጠንካራ ሥነ ምግባር፣ ሀገር ወዳድነት፣ ትሑትነት፣ ታማኝነትና ሐቀኛነት፤ ጠንካራ የመማር ትጋት/ተነሣሦት፤**

**ትብብራዊ መማር፤ በራስ ፍጥነት መማር፤ መስፈርትተኮር ምዘና፤ ተተኪ መፍጠር፤ ራስን መግዛትና በራስ መተማመን፤ ተማሪ አሳታፊ የትምህርት አስተዳደር፤ የተግባር ልምምድ፤ የግል ብቃትን ማስመስከር ናቸው፡፡**

በመጨረሻም በተዛማጅ ድርሳናት ንባባችን፣ በምልክታና በቃለ መጠይቅ መረጃዎቻችን እንደተረዳነው በቅድስት ቤተ ልሔም የድጓ ምስክር ትምህርት ቤት የድጓ ሥርዐተ ትምህርት ትኩረት ያላገኘ ስለሆነ የወደፊት ተመራማሪዎች ይህንኑ እንዲመረምሩትና በሥርዐት እንዲጽፉት እንጠቁማለን፡፡

**ዋቢዎች**


ባሕሩ ዘውዴ፡፡ (1984 ዓ.ም./1992)፡፡ የሦስት ሺ ወይስ የመቶ ዓመት ታሪክ? *ውይይት/Dialogue፣ 3/1*፤11-6

ገሪማና ሌሎች፡፡ (2009)፡፡*የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ 2000 ዓ.ም*፣ኹለተኛ እትም፡፡

ኅሐ ጽባሕ ወልደ ሐዋርያት፡፡ (1988 ዓ.ም.)፡፡ *መጽሐፈ ድጓ ዘቅዱስ ያሬድ*፡፡ አዲስ አበባ፤ ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፡፡

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡፡ (፲፱፵፰)፡፡ *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ መዝገበ ቃላት*፡፡ አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ሀብተ ማርያም ወርቅነህ፡፡ (1963 ዓ.ም.)፡፡ *ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት*፡፡ አዲስ አበባ፤ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡፡

ዘርዐ ዳዊት ፍሥሐ፡፡ (2011 ዓ.ም.)፡፡ *ይትበሀል ዘድጓ ምስለ ምሳሌሁ ወተአምሪሁ ምስለ ዐዋዲሁ*፡፡ አዲስ አበባ፡፡

ሙሉ ገላው፡፡ (1994 ዓ.ም.)፡፡ ፍሬ ሊቃውንት፡፡ *ስመዐ ጽድቅ ጋዜጣ*፣ መጋቢት 1994፡፡

መርሻ አለኸኝ፡፡ (2011 ዓ.ም.)፡፡ *በእንተ ስማ ለማርያም፤ ጥንታዊዉ የኢትዮጵያ ትምህርት ይዘቱ፣ ሥርዐቱ፣ ሕይወቱ*፡፡ አዲስ አበባ፤ ፋር ኢስት ትሬዲንግ፣ ኃ.የተ.የግ.ማኅበር

Atale Tilahun & Solomon Melese. (2022). An exploration into the practice of traditional church education in Ethiopia: Zema-bet education in focus. I. J. *Education and Management Engineering, Vol. 2*:7-20.

Ayele Bekerie. (2007). St, Yared-the great Ethiopian composer. *Tadias Magazin*, Nov. 29, 2007

Binns, J. (2005). Theological education in the Ethiopian Orthodox Church. *The Journal of Adult theological Education, 2/2*:103-113.

Binns, John. (2013). Out of Ethiopia – a different way of doing theology. *International journal for the Study of the Christian Church, 13:1*, 33-47, DOI: 10.1080/1474225X.2012.754137

Chaillot, C. (2009). *Traditional teaching in the Ethiopian orthodox church: yesterday, today and tomorrow. Proceedings of the 16th International Conference of Ethiopian Studies*, ed. by Svein Ege, Harald Aspen, Birhanu Teferra and Shiferaw Bekele, Trondheim

Firdyiwok Abebe Yehuwala1 & Ertiban Demewoz Molla. (2018). Challenges and opportunities for safeguarding traditional church schools as cultural heritage center: The case of three selected schools, South Gondar Zone, Ethiopia. *Journal of Tourism & Hospitality፣ 7:5*፣ 10.4172/2167-0269.1000382

Girma Amare. (1967). Aims and purposes of church education in Ethiopia. *Ethiopian Journal of Education, 1/1*: 1-11.

Haile Gebriel Dagne. (1971). The traditional Ethiopian curriculum. *The Ethiopian Journal of Education, 4/2*:79-82.

Hailu Fulas. (1974). Knowledge and its attainment in the Ethiopian context. *The Ethiopian Journal of Education, 7/1*:19-24

Mengesha Robso. (2021). Where indigenous knowledge is beyond modernity: an experience from the ethiopian orthodox church traditional adult education practices, Ethiopia. *PJAEE, 18 (1)*, 4143-4160.

Mezmur Tsegaye. (2011). *Traditional education of the Ethiopian Orthodox Church and its potentioal for tourism development (1975-present).* [Addis Ababa University unpublished M.A thesis]. www.academia.edu/2446790

Molla Bekalu Mulualem, Alemayehu Bishaw Tamiru & Asrat Dagnaw Kelkay. (2022). Traditional educational systems in Ethiopia: A pedagogical practices inquiry, *Review of Education, Pedagogy, and Cultural Studies*, 44:3, 281-99, DOI: 10.1080/10714413.2021.1985373

Paulos Milkias. (1976). Traditional institutions and traditional elites: the role of education in Ethiopian body-politic. *African studies review, 19:3*, 79-93. http://www.jstor.com/stable/523876

Selamsew Debashu. (2017). *The Teaching-learning Processes in the Ethiopian Orthodox Church Accreditation Schools of Music (Zema Bets): Addis Ababa University: The Cases of Bethlehem, Zur Aba and Gondar Baeta Mariam Churches*. [A thesis submitted to the centre for African and oriental studies]

Setargew Kenaw. (2004). Studying traditional schools of the Ethiopian orthodox church: a quest for fresh methodology. *Ethiopian Journal of the Social Sciences and Humanitie, 2:1*, 107-122, https://www.ajol.info/index.php/ejossah/article/view/29861

Shelemay, K.K. (1992). The musician and transmission of religious tradition: the multiple roles of the Ethiopian Debtra. *Journal of religion in Affric, XXII*, 3: 242-260.

Taddesse Tamirat. (1985). A short note on Ethiopian church Music. *Annales d'Ethiopia, vol.13*: 137-143. https://www.persee.fr/doc/ethio_0066-2127_1985_num_13_1_928

Tebeje Molla. (2018). Higher education in Ethiopia: structural and inequalities and policy responses chapter 2. *Springer*, https://doi.org/10.1007/978-981-10-7933-7_2

Teksete Negash. (1996). *Rethinking education in Ethiopia*. Sweden: Reprocentralen HSC, Uppsala.

Wube Kassaye. (2018). Education of Ethiopian Orthodox church: Personal reflection on Nibabe Bet and Zema Bet. *Journal of church studies, No.6*

Yared Nigussie Demssie, Biemans, H.J.A.; Mulder, M.& Wesselink, R. (2020). Combining indigenous knowledge and modern education to foster sustainability competencies: towards a set of learning design principles. *Sustainability,* www.mdpi.com/journal/sustainability.